አፍሪካ ቲቪ

5

# አፍሪካ አካዳሚ
# AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

## ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት አዝካር ፣ ዱዓዕ እና ከፍተኛ ምንዳ ያላቸው ሥራዎች

5

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

# ዱዓዕ

- ሁሉም ፍጡር ወደ አላህ (ﷻ) ከጃይ (ከአሏህ ፈላጊ) ነው፡፡
- እሱ ዘንድ ያለው ነገር ያስፈልገዋል፡፡ እሱ ደግሞ ከፍጡራኑ የተብቃቃ ነው፡፡
- አላህ (ﷻ) ባሮቹን እንደሚለምኑት:- **(ጌታችሁም አለ፡፡ ለምኑኝ እቀበገላችኋለሁና፡፡ እነዚያ እኔን ከመገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ሆነው ገሀነምን ይገባሉ፡፡)** 40፡60 በማለት እንዲለምኑት ግዴታ አድርጓል፡፡
- ነብዩ ሙሀመድም (ﷺ) ኢብኑ ማጃህ በዘገበው ሀዲስ **(አላህ ልመናውን የተወን ሰው ይቆጣበታል)** ብለዋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ከዚህም ጋር አላህ (ﷻ) አገልጋዩን ሲለምነው ይደሰታል፡፡ እሱን በመለመን ችክ ባዮችንም ይወዳል፡፡ ወደራሱም ያቀርባቸዋል፡፡

- የነብዩ ﷺ ባልደረቦችም ይህን እውነታ ተረድተውት የትኛዋንም አነስተኛ ጉዳይ አላህን (ﷻ) ከመጠየቅ አይንቁም ነበር፡፡ ጨው እንኳ ቢያጣ፤ የጫማ ክር እንኳ ሲበጠስበት፤ የትኛውንም ጉዳይ ለአላህ እንጂ ለማንም ተራ ፍጡር አያቀርቡትም ነበር፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው **(ባሮቼ ከኔ በጠየቁህ ጊዜ በላቸው - እኔ ቅርብ ነኝ ፤ የለማኝን ፀሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ፡፡)** ባለው ቁርአናዊ አባባል መሰረት እነሱ በጌታቸው ላይ ካላቸው የሙጢኝ (ችክ) ባይነት፤ ወደ አላህ (ﷻ) ካላቸው ቅርበትና እሱም ወደነሱ ካለው ቅርበት እንጂ ሌላ አይደለም፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ዱዓ በአላህ (ﷻ) ዘንድ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ነው፡፡
- በአላህ (ﷻ) ዘንድ ትልቅ ክብር እና ትልቅ ቦታ አለው፡፡ የአላህንም ቀደር (ውሳኔ) ሊመልስ (ሊቋቋም) ይችላል፡፡ የሙስሊም ዱዓ ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉና እንቅፋቶች ከተወገዱለት ሁልጊዜም ተቀባይነት አለው፡፡
- ዱዓ የሚያደርግ ሰው አህመድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሀዲስ ነብዩ (ﷺ) **(ማንም ሙስሊም ወንጀል ወይም ዝምድናን መቁረጥ ያልተቀላቀለበት ዱዓ ካደረገ ከሶስት ነገሮች አንዱ ይሰጠዋል፡፡ የለመነው በዚሁ በዱንያ ህይወት ሊፋጠንለት፤ ወይም ወደ አኺራ ተላልፎ ሊቀመጥለት ወይም ሊያገኘው የነበረውን ክፉ ነገር በዱዓው አቅም ልክ ሊከላከልለት ነው፣ ሲሉ ሰሀቦችም እንግዲያውማ - እናብዛ ማለት ነው - ሲሏቸው - የአላህ ፀጋ ይበዛል)** በማለት መልሰውላቸዋል፡፡

- **የዱዓዕ አይነቶች ሁለት ናቸው፡፡**

1) አምልኮታዊ ዱዓዕ፡- ሰላትና ፆም የመሳሰሉት፡፡

2) የልመና እና የጥያቄ ዱዓዕ፡፡

- **ተግባሮች አንዱ ከሌላው ስለመበላለጣቸው፡፡ ቁርኣን ማንበብ** ወይስ **ዚክር** ወይስ **ዱዓ** ይበልጣል? ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ቁርአን ማንበብ ከሁሉም ኸይር ስራ ይበልጣል፡፡ ከዛም ዚክር ይከተላል፡፡ ከዚያም ዱዓ ይቀጥላል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለው ቅድሚያ ሊሰጠው የሚችለበት ጊዜ አለ፡፡ ለምሳሌ የአረፋ እለት ዱዓ ማድረግ ቁርአንን ከማንበብ ይበልጣል፡፡ ከየፈርድ ሶላቶች ቡኋላ ከነብዩ በተዘገቡት ዚክሮች ላይ ማተኮር ደግሞ በዚያ ሰአት ቁርአንን ከማንበብ ይበልጣል፡፡

- * ለዱዓ ተቀባይነት ምክንያቶችና መስፈርቶች፡- እዚህ ላይ ግልፅና ድብቅ ምክንያቶች አሉ፡፡

- 1. ግልፅ ምክንያቶች... መልካም ስራዎችን ማስቀደም፣ ለምሳሌ ሰደቃ፣ ውዱእ፣ ሰላት፣ ወደ ቂብላ መዞር፣ እጆችን ማንሳት፣ አላህን (ﷻ) በተገቢው ሁኔታ ማወደስ፣ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የአላህ (ﷻ) ስሞችና ባህሪያት እያነሱ መለመን፤ ለምሳሌ ጀነትን የሚለምን ሰው የአላህን ቱሩፋት የሚያሳዩ እና የሚያመለክቱ ስሞችንና ባህሪያትን ማውሳት፣ ግፍ በዋለበት ላይ የሚለምን ከሆነ ደግሞ መጠቀም ያለበት ጀባር ቀሃር (ሀያሉ ጌታ)... የመሳሰሉትን **ስሞችና ባህሪያትን በማውሳት፤** በዱዓው መግቢያ በመሀከሉና በመጨረሻው ላይ በነብዩ ሰ.ዐ.ወ
 ላይ ሶለዋት ማውረድ፤ በሰራው ወንጀል ማመን፣
 የአላህን ውለታ ማመስገን፣

- ዱዓዕ ተቀባይነት ይኖረዋል የተባለባቸውን ሰአቶችና ቦታዎች መምረጥ ሲሆን እነሱም ብዙ ናቸው፡፡ ከብዙ በጥቂቱ:-
- * **በቀንና በለሊት ውስጥ የሚገኙ፡- አላህ ወደ ቅርቢቱ ሰማይ በሚወርድበት በመጨረሻው አንድ ሦስተኛ የሌሊት ክፍል፤** በአዛንና በኢቃማ መካከል፤ ከውዱእ ቡኋላ፤ በሱጁድ ላይ እያለ፤ ከሶላት ማሰላመት በፊት፤ ከየሶላቶቹ ቡኋላ፣ ቁርአን በሚኸተምበት ጊዜ፤ ዶሮ ሲጮህ፤ በመንገድ ላይ እያሉ (ሙሳፊር ሰው) ዱአ፤ የተበደለ ሰው ዱዓ የተቸገረ ሰው ዱዓ፤ አባት ለልጁ የሚያደርገው ዱዓ፤ ሙስሊም ወንድሙ በርቀት ለሌለው የሚያደርግለት ዱዓ ከጠላት ጋር ሲገናኙ የሚደረግ ዱዓ ናቸው፡፡
- * **ከሳምንት ውስጥ - የጁምዓ እለት** በተለይም በቀኑ የመጨረሻዋ ሰዓት ላይ፤
- * **ከወሮች ውስጥ - በረመዷን ወር** በፊጥርና በሱሁር ሰዓት፤ ለይለተል ቀድርና፤
- * **የአረፋ ቀን ናቸው፡፡**

- የተከበሩ ቦታዎችን በተመለከተ በአጠቃላይ መስጂዶች በተለይም በመካ ካዕባ አጠገብ፤ ሙልተዘም ዘንድ፤ ካዕባ መቃሙ ኢብራሂም (የኢብራሂም መቆሚያ ዘንድ)፤ ሰፍዋ እና መርዋ ላይ፤ በሐጅ ጊዜ በአረፋ፣ በሙዝደሊፋና በሚና ላይ፤ የዘምዘምን ውሀ በሚጠጡበት ጊዜ እና በሌሎችም ቦታዎችና ሰዓቶች ነው፡፡

- 2. **ድብቅ ምክንያቶች-** እነኚህም፡- እውነተኛ ተውበትን ማስቀደም፤ በበደል የወሰዱትን ነገር መመለስ፤ ምግብን፤ መጠጥን፤ ልብስንና፣ መኖሪያን ማሳመርና ከሀላል ማድረግ፤ ኢባዳን ማብዛት፤ ወንጀሎችን መራቅ፤ ከሹቡሀዎችም/ ከአጠራጣሪ ነገሮችም/ ሆነ ከስሜቶች ነፃ መሆን፤ በዱዓእ ጊዜ- ዱዓን ከልብ ማድረግ፤ በአላህ (ሱ.ወ) መተማመን፣ የተስፋ ስሜትን ማዳበር፤ ወደ አላህ መጠጋት፤ ራስን ማስተናነስና በአላህ (ሱ.ወ) መለመን ላይ ችክ ማለት፣ ሁሉን ነገር ወደ እርሱ ማስጠጋትና ከሱ ሌላ ከሆኑ ሁሉ ተስፋ መቁረጥ ናቸው፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- **ዱዓን ተቀባይነት የሚያሳጡ ነገሮች፡-** የሰው ልጅ አንዳንድ ጊዜ ዱዓ አድርጎ ተሰሚነት ያጣ ይሆናል፡፡ ወይም ይዘገይበት ይሆናል፡፡ ታድያ የዚህ ምክንያቶቹ ብዙ ናቸው፡፡ ከእነርሱም ውስጥ
- * ከአላህ ጋር ሌላን አካል መጣራት (ሽርክን መፈፀም)፤
- *በልመናው ውስጥ ዝርዝር ነገሮችን መጥቀስ፡- ለምሳሌ ከእሳት ጠብቀኝ የሚለው በቂ ሁኖ ሳለ ከጀሀነም ከጥበቷ፤ ከጨለማዋ ጠብቀኝ ማለትን ይመስል፤
- * አንድ ሰው በራሱ ላይ ወይም በሌላው ላይ በግፍ ዱዓ ማድረግ፤
- * በወንጀልና ዝምድናን በመቁረጥ ዱዓ ማድረግ፤

- * ልመናውን ከፈለከ አድርግልኝ ስትፈልግ ማረኝ ... ብሎ መለመን፤
- * ዱአ አድርጌ ነበር ነገር ግን ተቀባይነት አላገኘሁም በማለት መልሱን ለማግኘት መቸኮል፤
- * ዱዓ ከማድረግ መሰላቸት፤
- * በተዘናጋ ልብ ዱአ ማድረግ፤
- * ከአላህ ፊት ተገቢውን ስርዓት አለመያዝ፤ እና የመሳሰሉት ዱዓን ተቀባይነት ከሚያሳጡ ነገሮች ናቸው፡፡

- ነብዩ (ﷺ) አቡዳውድና ቲርሚዚይ በዘገቡት ሀዲስ **(አንድን ሰው በሶላት ውስጥ በርሳቸው ላይ ሶለዋት ሲያወርድ ዱዓ ሲያደርግ ሰምተውት (ይህ ሰው ቸኮለ) አሉና እሱን ጠርተው ወይም ለሌላ ሰው (ማንኛውም ሲሰግድ በመጀመሪያ አላህን በማመስገንና በማወደስ ይጀምር፤ ከዚያም በነብዩ ላይ ሶለዋት ያውርድ፤ ከዚያም የፈለገውን ይጠይቅ)** ብለዋል፡፡ አቡዳውድና ቲርሚዚ ዘግበውታል፡፡
- ሊሆን የማይችልን ነገር መለመን፣ ለምሳሌ በዚህች አለም ላይ ለዝንት አለም አኑረኝ ማለት፣
- በግድ በግጥም መልክ ለማድረግ መልፋት ተገቢ አይደለም፡፡ ምክንያቱም አላህ እንዲህ ብሉዋል፡፡ (ጌታችሁን ተናንሳቹህና ተዋርዳችሁ በድብቅ ለምኑት፤ እርሱ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና፡፡) ቡኻሪ በዘገቡት ሀዲስ ኢብኑ አባስ ስንኝ ያለበትነ ዱዓ እያየህ ራቀው፡፡ ነብዩና ባልደረቦቻቸውን ያገኘሁት እንዲህ ያለውን ዱአ ሲርቁ ነው ብለዋል፡፡
- ድምፅን ከመጠን በላይ ማጉላት አይገባም፡፡ አላህ (ﷻ) እንዲህ አለ
 (በስግደትህ (ስታነብ) አትጬህ፡፡ በእርሷም ድምፅህን ዝቅ አታድርግ
 በሁለቱ መካከል መንገድ ያዝ፡፡) እናታችን አይሻ እንደሚሉት - ይህ የወረደው
 በዱዓ ምክንያት ነው ብለዋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- በኢስላም ከሚወደዱ ነገሮች አንዱ ዱዓ የሚያደርግ ሰው፡፡ ከዱዓዕ ኣዳቦች፡-
- **በመጀመሪያ** - አላህን ማመስገንና ማወደስ፤
- **በሁለተኛ** - ለነብዩ (ﷺ) ሶለዋት መለመን፤
- **ሦስተኛ**- ወንጀለኛ መሆንን ማመን፤
- **አራተኛ**- አላህን (ﷻ) ስለፀጋው ማመስገን፤
- **አምስተኛ**- ወደ ዱዓው ገብቶ ከነብዩና ከሰለፎች ከተዘገቡት ዱዓዎች መካከል ብዙ ነገሮችን ሊያጠቃልሉ የሚችሉ ጠቅላይ ዱዓዎችን በተቻለ መጠን መምረጥና፤
- **ስድስተኛ**- ዱዓውን በነብዩ ሙሀመድ (ﷺ) ላይ ሶለዋት በማውረድ ማጠናቀቅ ነው፡፡